

# አዲስ ዝማሬ እንዘምር

በወይዘሮ ውሂብ ዘውዴ

«በእንግድነቴ ሃገር ሥርዓትህ መዝሙሬ ናት።» (መዝሙር 119፥54) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት የእምነት አባቶች የዚችን ዓለም ኑሮ ያዩት እንደ ጊዜያዊ መጠለያ ነበር። ለዚህ ነው ከላይ ባየነው ጥቅስ ላይ ዳዊት «በእንግድነቴ ሃገር» ማለት በጊዜያዊው መጠለያዬ (መኖሪያዬ) ሥርዓትህ፣ ቃልህ፣ ትዕዛዝህ፣ ሃሣብህ፣ ፈቃድህ፣ እውነትህ፣ ሕግህ፣ ዓላማህ «መዝሙሬ ነው» ያለው።

የቀደሙት የእምነት አባቶች በምድር ላይ ለብዙ ዓመታት ኖረዋል፤ ነገር ግን ከዘለዓለም ጋር ሲያነፃፅሩት የምድር ኑሮአቸውን ያዩት በእንግድነት ለጊዜው የሚኖሩበት እንደሆነ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ዕድሜያችን ሰባ ዓመት ነው ፣ ቢበዛም ሰማንያ ዓመት ነው። እርሱም በመከራና በሐዘን የተሞላ ነው። እድሜያችን በቶሎ ያልቃል፣ እኛም እናልፋለን።» ይላል። (መዝ. 90፥10) በዚህ በአጭሩ ዕድሜአችን የእግዚአብሔርን እውነት እየዘመሩ መኖር እንዴት መልካም ነው!!

ዝማሬ (ሙዚቃ) የመነጨው ከምድር ሳይሆን ከሰማይ ነው። እግዚአብሔር ገና ፍጥረትን ሲፈጥር በዝማሬ ታጅቦ ነበር ማለት እንችላለን። ኢዮብ 38፥1-7 ላይ ምድር የተመሠረተችው መላእክትና ከዋክብት እየዘመሩ እንደነበር ይናገራል። ምናልባት፣ «አቤት ሥራህ፣ ያንተ ሥራ፣ ያምላክ ሥራ አይወራ። አቤት አንተ ጥበብህ፣ ዕውቀትና ችሎታህ።» እያሉ ይሆናል የዘመሩት።

ዝማሬን ለመላእክትም ሆነ ለሰው የሰጠ እግዚአብሔር ራሱ ነው። ነገር ግን እንደ ማንኛውም ስጦታ ሁሉ ሰው የተሰጠውን ስጦታ ለክፋት ወይም ለበጎ ነገር (ለእግዚአብሔር ክብር) ሊጠቀምበት ይችላል።

ሙዚቃን (ዝማሬን) በትክክለኛው መንገድ በመጠቀም በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ሲኖረው በሚከተሉት ሁናቴዎች ውስጥ እንመለከታለን ። ነቢዩ ኤልሣዕ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ተጠቅሞበታል። (2ኛ ነገሥት 3፥14-15) የነቢያት ጉባዔ በሙዚቃና በዝማሬ ታጅበው ይተነብዩ ነበር። (1ኛ ሣሙኤል 10፥5-6) ንጉሥ ሳዖል ዳዊት በገና ሲደረድርለት ይዞት የነበረው ክፉ መንፈስ ይለቅቀው ነበር። (1ኛ ሣሙኤል 16፥14-16) በሰለሞን መቅደስ መዘምራን ሲዘምሩ የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠ። (2ኛ ዜና መዋዕል 5፥12-14)

በዝማሬ ጳውሎስና ሲላሥ ወኅኒ ቤት ታሥረውበት የነበረው ሠንሠለት ተበጥሷል። (የሐዋርያት ሥራ 16፥25-26) ጌታ ኢየሱስ ራሱ ለመሰቀል ሲዘጋጅ ዘመረ። (ማቴ. 26፥30) (በችግር ጊዜም መዘመር እንደምንችል ምሳሌን ሲተውልን ነው።)

ሙዚቃ (ዝማሬ) የነፍስ ቋንቋ ነው። በየዘመኑ ያሉ ሰዎች ሁሉ የውስጥ ስሜታቸውን ለመግለፅ ቋንቋውና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ዘምረዋል (አዚመዋል)። ይሁን እንጂ ትክክለኛው ዝማሬ አማኞች እግዚአብሔርን ለማክበር የሚዘምሩት ነው። አማኞች ከነፍሳቸው የወጣ ዝማሬን የሚያቀርቡት ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ነው። ክርስቲያኖች የምንዘምረው የቃላት ግጥም ቤት ስለመታልንና ሙዚቃ ስለጨኸልን አይደለም። የዝማሬአችን ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ለማክበር ነው። ከዚህ ቀጥሎ ስለአማኞች መዝሙር ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን እንመለከታለን።

1) የዝማሬያችን ምክንያቶች
2) የዝማሬያችን ዓይነቶች
3) የዝማሬያችን አድማጮች (ተቀባዮች)።

1) የዝማሬያችን ምክንያቶች

የምንዘምረው ለልማድ አይደለም፤ የሚያዘምሩን ምክንያቶች ስለአሉን ነው። ከብዙ ምክንያቶቻችን ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) የእግዚአብሔር ምሕረት

ለአንዲት የዳነች ነፍስ ትልቁ የዝማሬ ምክንያት «የእግዚአብሔር ምሕረት» ነው። የዳንነው ከምሕረቱ የተነሣ ነው። (ቲቶ 3፥5) ዳዊት፣ «የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት በዘመኔ ሁሉ ይከተሉኛል።» ሲል ይዘምራል። እኛም የዚህ ዘመን ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ዘምረን መጨረስ አንችልም።
ለዚህ ነው፥
ከተስፋዬ ጋቢሶ ጋራ፣ «ምሕረቱ አያልቅምና ለዘላለም ቸር ነውና።» እያልን የምንዘምረው።
ከዳንኤል አምደ ሚካኤል ጋር፣ «ምሕረቱ እያስደነቀኝ፣ ለጌታዬ መዝሙር ባመጣ ...» የምንለው።
ከሊ.ሊ. ጋር ደግሞ፣ «ምሕረቱ ይጎተጉተኛል፣ ተነሺ አመስግኝ ይለኛል፥ ... » በማለት የምንዘምረው።

ለ) እግዚአብሔር ቀድሞ ያደረገልን ውለታ

ሌላው ምክንያታችን ባለፉት ዘመናችን እግዚአብሔር ያደረገልንን ውለታ ስላለ ነው። ዳዊት በመዝሙር 40 ቁጥር 2 ላይ፣ «ከሚውጥ ጉድጓድ፣ ከሚያዘቅጥ ማጥ አወጣኝ፤ እግሮቼን በዓለት ላይ አቆመ፣ አካሄዴንም አፀና።» ይላል። ሁላችንም ከመዳናችን በፊት በሚሰቀጥጥ ጉድጓድ ውስጥ ነበርን። ጌታ ኢየሱስ ከሚያሰጥም የኃጢአት ረግረግ ጭቃ ውስጥ ነው ያወጣን። ከዚህ ጉድ የዳነ አማኝ ቢዘምር ሲያንስበት ነው። ለዚህ ነው የምንዘምራቸው ዝማሬዎች የሚከተሉትን ሃሣብ የሚያንፀባርቁት፥-

«... ከግር ብረት ተፈታሁ፣ ነፃነት አገኘሁ ...»
«እግዚአብሔር ይመስገን ከውድቀት አነሳኝ...»
«ወጥመዱ ተሰበረ፣ እኛም አመለጥን ...»
«አመለጥኩኝ፣ ከአዘቅት ወጣሁኝ ...» ወዘተ.

እግዚአብሔር ከደኅንነታችንም ሌላ ባለፉት ጊዜያት ያደረገልንን ውለታ ሁሉ እያስታወስን በዝማሬ እንወድሰዋለን፣ እናመሰግነዋለን።

ሐ) እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የሚያደርግልን ውለታ
እግዚአብሔር የታሪክ ብቻ አምላክ አይደለም። ጌታ በየዕለቱ የሚያደርግልንን ውለታ በማሰብም በዜማ እናመስግነዋለን (እንዘምርለታልን)። እግዚአብሔር ጠባቂያችንና የረድኤታችን ሁሉ ምንጭ ስለሆነ እናመሰግነዋለን። ዳዊት በመዝሙር 91፥11-12 ላይ፤ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋልና፣ እግርህን ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ በእጆቻቸው ወደ ላይ ያነሡሃል።» ይላል። እግዚአብሔር በየቀኑ መውጣት መግባታችንን ስለሚቆጣጠርና ከክፉ ሁሉ እየከለለ በመልካሙ መስክ ስለሚያሰማራን ይህንን ውለታ ሁሉ እያሰብን ለክብሩ እንዘምራለን።

2) የዝማሬአችን ዓይነቶች

ሀ) <u>አዲስ ዝማሬ</u>

ዝማሬን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው ብለናል። ይህ ከሆነ እግዚአብሔር የሚሰጠው ዝማሬ ምን ዓይነት ነው? መዝ. 40 ቁጥር 3 ላይ እንዲህ ይላል፥-

«ለአምላካችን የሚሆን ውዳሴ አዲስ ዝማሬን በአፌ ላይ አኖረ። ብዙዎች ያያሉ፣ ይፈራሉም በእግዚአብሔርም ይታመናሉ።»



ከጥቅሱ እንደምንረዳው እግዚአብሔር አዲስ ዝማሬን ይሰጣል ። «አዲስ ዝማሬ» ካለ ደግሞ «አሮጌ ዝማሬ» አለ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17 ላይ፥-

«ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው።» ይላል። ጥያቄው፣ «አዲስ ፍጥረት ሆነናል (ድነናል) ወይ?» ነው። ከአዲሱ ሰው የሚወጣው አዲስ መዝሙር ነው። በክርስቶስ ከተለወጥን በኋላ ዓለም ውስጥ እንኑር እንጂ ሰማያዊ ዜግነትና ቋንቋ ተሰጥቶናል። በሕይወታችን ያገኘነው አዲስ ለውጥ የመዝሙራችንን ዓይነትም ይለውጣል።



አሮጌው ፍጥረት ይዘምር የነበረው የዓለም መዝሙር (ዘፈን) ምንም ያህል እንኳ የደመቀና ጭፈራም የበዛበት ቢሆን በውስጡ የሚተላለፈው መልእክት፣ እግዚአብሔርን የሚያስከፋ፣ ወደ ክፋትና የዝሙት ርኩሰት የሚገፋፋ፣ ሰውን ወይም ሠይጣንን ራሱን የሚያሞጋግስ ነበር። መቼም ከጠቢቡ ሰለሞን የበለጠ የሥጋን መንገድ (የአሮጌውን ሰው መንገድ) የተከተለ ሰው የለም ። ሰለሞን ሥጋውን ለማርካት ብዙ ደክሟል። መክብብ 2 ቁጥር 8 ላይ፣

« ... ለራሴም ወንድና ሴት አዝማሪዎች ነበሩኝ።» ይላል።

ከዚሁ ምዕራፍ ሳንወጣ ቁጥር 10ና 11 ላይ ግን እንዲህ በማለት ይናገራል፥-

«ዓይኔ የፈለገውን ሁሉ አልከለከልሁትም፣ ለልቤም ምድራዊ ደስታን አልነፈግሁትም፣ ልቤ በሠራሁት ሁሉ ደስ አለው፣ ይህም የድካሜ ሁሉ ዋጋ ነበር። ሆኖም እጆቼ የሠሩትን ሁሉ ለማግኘት የደከምሁትን ድካም ሁሉ ሳስብ ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነበር። ከፀሐይ በታች ምንም ትርፍ አልነበረም።»

አዲሱ ፍጥረት ለፍጡር ሳይሆን ለፈጣሪ ይዘምራል። የተፈጠረውን ሳይሆን ፈጣሪን ያመልካል። (ሮሜ 1፥25) ጌታ ኢየሱስን ብቻ ያሞጋግሳል፣ ያከብራልም። ዘማሪዋ እንዳለች፥-

«እኔ አፌን አልከፍትም ለዓለም ክብር
እዘምራለሁኝ ለእግዚአብሔር።»

ክርስቲያኖች በእርግጥ አዲስ ዝማሬ ተሰጥቶናል። በክርስቶስ የተዋጀችው የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን አዲስ ዝማሬ ዘምረዋል። -

«እንዲህም እያሉ አዲስ መዝሙር ዘመሩ፥
መጽሐፉን ልትወስድ፣ ማኅተሙንም ልትፈታ
ይገባሃል፤ ምክንያቱም ታርደሃል፣
በደምህም ከነገድ ሁሉ ከቋንቋ ሁሉ
ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ
ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል።
ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት አድርገሃቸዋል፥
እነርሱም በምድር ላይ ይነግሣሉ።» ራዕይ 5፥9

ለ) የደስታ ዝማሬ

ሌላው እግዚአብሔር የሚሰጠን መዝሙር «የደስታ ዝማሬን» ነው። በዘፈንና መዝሙር መካከል ያለው ልዩነት የቃሉ መልእክት ነው። የዘፈን መልእክት ዝሙትን ፣ አመፅን፣ ሱስን፣ ግድያን፣ ወዘተ... ያደፋፍራል። የዳኑ ሰዎች መዝሙር ግን ሕይወትን የሚሰጥ፣ የሰላም፣ የደስታና የምሥጋና መልእክት ያለው ነው።

በተጨማሪም የክርስቲያን መዝሙር ተስፋ አስቆራጭ የሃዘን እንጉርጉሮ፣ «አይ ዕድሌ ...»፣ «አይ የኔ ነገር!» «ወዮልኝ!» ወዘተ) ሳይሆን ተስፋና ድል ያለበት ነው። ዝማሬያችን ደስታችንንና ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚገልፅ ነው።

«ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ ዘምሩ
ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።
ለእግዚአብሔር ዘምሩ ስሙንም ባርኩ
ማዳኑንም ነጋ ጠባ አውሩ።
ክብሩን በሕዝቦች መካከል
ድንቅ ሥራውንም በሰዎች ሁሉ ፊት ተናገሩ።
እግዚአብሔር ታላቅ ነውና ውዳሴም የሚገባው ነው።
ከአማልክት ሁሉ በላይ ሊፈራ ይገባዋል።
የአሕዝብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው።
እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
ክብርና ግርማ በፊቱ ናቸው
ብርታትና ውበትም በመቅደሱ ውስጥ አሉ።»

ሐ) የሌሊት ዝማሬ

«እግዚአብሔር ... በሌሊት መዝሙርን የሚሰጥ።» ኢዮብ 35፥10

የሰው ነፍስ (አእምሮ፣ ፈቃድንና፣ ስሜትን ያካትታል)። ከሁናቴዎች ጋር ከፍና ዝቅ የማለት ዝንባሌ አለው። ቀን ሲሆን መዘመር ይቀለናል። ሲጨልም የደስታ መዝሙር መዘመር ይከብደናል። የአማኝ መዝሙር ግን በሁናቴ ላይ የተመሠረተ አይደለም። በቀንም ሆነ በሌሊት ጊዜ ለእግዚአብሔር ክብር መዘመር ይቻላል። ሰማዩ ቢጨልም፣ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃንም ባይታይ አማኝ ይዘምራል። ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላኩ በለሊትም መዝሙርን ይሰጠዋልና። ዓይነቱና ጊዜው ይለያይ እንጂ በሁላችንም ሕይወት ውስጥ የጨለማ (የችግር) ጊዜ ይመጣል። የቱንም ያህል ችግር ቢያጋጥመን የትኛውም ችግራችን ከእግዚአብሔር ታላቅነት ስለማይበልጥ ለእግዚአብሔር ክብር ከመዘመር አያግደንም። ምክንያቱም የአማኝ መዝሙር ከውጪያዊ ሁኔታ የሚመጣ ሳይሆን ከውስጥ የሚመነጭ ነው።

## 3) የዝማሬያችን አድማጮች(ተቀባዮች)

ሀ) እግዚአብሔር፥-


የመጀመሪያው የዝማሬያችን አድማጭ እግዚአብሔር ነው። አማኞች የምንዘምረው ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ነው። (መዝሙር 96፥1-3፣ ኤፌሶን 5፥19፣ ዕብራውያን 13፥15፣ ቆላስይስ 3፥16)

ቃሉ፣ «ለእግዚአብሔር ተቀኙ።» ይላል። የምሥጋና መሥዋዕት በዝማሬ የምናቀርበው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። የምንዘምረው የኛን ስሜት ለማርካት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር ነው።

ለ) የማያምኑ ሰዎች

ለማያምኑ ሰዎች ለመመስከር መዝሙር ስብከትን ባይተካም የወንጌልን ስብከት የሚደግፍ ከፍተኛ አገልግሎት ነው። መዝሙር የሰዎችን ልብ ለቃሉ ያዘጋጃል። ወደ እግዚአብሔር ሕልውናም ለመግባት በርን ይከፍትልናል። ዘማሪው ዳዊት፣

«በምስጋና ወደደጆቹ፣ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ፣ አመስግኑት ስሙንም ባርኩ።» ይላል።



ሐ) <u>ቤተ ክርስቲያን (አማኞች)</u>

ሁሉም መንፈሳዊ መዝሙሮች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ናቸው። ሆኖም የምንዘምራቸው ዝማሬዎች፥

1) አማኞችን (ቤተክርስቲያንን) ለመምከር፣ ለማነፅ፣ ለማስተካከልና ለማበረታታት ይጠቅማል።

2) ለማስተማር፥- እያንዳንዱ ዝማሬ ትምህርት አለው። ስለዚህ መዝሙራችን እንደ
3) እግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት። ዝማሬያችን በእግዚአብሔር እውነት ላይ መመሥረት ይኖርበታል። በመዝሙር «እውነትን» እንናገራለን፣ እናስተምራለንም።

ለማጠቃለል፥- መዝሙር ዋና ዋና ከሆኑ የክርስቲያን ልምምዶች አንዱ ነው። ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የእግዚአብሔር ልጆች ደስታ የሞላበት ዝማሬ ሲያቀርቡ እንደኖሩ ከታሪክ እንረዳለን። የአማኞች ዝማሬ ሌላው ቀርቶ በሙዚቃ ጥራቱና በዜማ ቅንብሩ እንኳን ከዓለም ዘፈን የበለጠ እንጂ ያነሰ መሆን የለበትም። መዝሙረኛው ዳዊት፣

«አዲስ መዝሙር ዘምሩለት
<u>በገናውን ባማረ ቅኝት ድርድሩ</u>
<u>እልልም በሉ።» ይላል።</u> መዝሙር 33፥3

በጥቅሉ መሠረት በተለይ በመዝሙር አገልግሎት የተሠማሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ዝማሬ እንደ ነገሩ መሆን የለበትም። ቅኝቱ ያማረ፣ መልእክቱም ሆነ ዜማው የጠራና መዝሙሩ ከመቅረቡ በፊት በደንብ የተጠናና ዝግጅት ያለበት መሆን ይገባዋል። ልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎችንም በመጠቀም ልንዘምር እንችላለን።

መዝሙር 150 ላይ በምን ዓይነት መሣሪያዎች ታጅበን ለእግዚአብሔር ክብር መዘመር እንደምንችል ዝርዘሩን ይሰጠናል።

1) በመለከት ድምፅ
2) በበገና
3) በመሰንቆ
4) በከበሮ
5) በሸብሸባ
6) በባለ አውታር መሣሪያ
7) በእምቢልታ
8) ተርገብጋቢ ድምፅ ባለው ፅናፅል
9) ድምፀ መልካም በሆነ ፀናፅል።

የእግዚአብሔር ልጆች የሰማዩ አባታቸውን ለማክበር ከሌሎቹ አስፈላጊ የክርስቲያን ልምምዶች ጋር አዲስ የሃሴትና የደስታ ዝማሬን ጥራትና ውበት ባለው መንገድ በመዘመራቸው መታወቅ አለባቸው።